# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ጥቅምት 11 ቀን 2004 ዓ.ም.**

**የወያኔ ቡድን ከፍተኛ ባለስልጣናቱን ከስልጣናቸው አባረረ፤**

**የቤንሻንጉል ክልል ፕሬዝዳነት የነበረው ያረጋል አይሸሹም ታሰረ፤**

**የህክምና ባለሙያዎች የወያኔን ቡድን አስጠነቀቁ**

በአዲስ አበባ ከተማ የተጀመረው የምንጠራ ዘመቻ ከፍተኛ የከተማዋን ባለስልጣኖች ጭምር ጠርጎ ያባረረ ሲሆን ወደ ዝቅተኛ ባለስልጣናትም እየወረደ መሆኑ ታወቀ::

ኩማ ደመቅሳን ጭምር እንዲቆጣጠር ከብአዴን የመጣው ምክትል ከንቲባ ከፍያለው አዘዘ ከስልጣኑ ከተነሳ በሁዋላ የአዲስ አበባ ከተማ በሹም ሽረት እየታመሰ መሆኑ ታውቆዋል::

የአምስት ዓመቱን የትራንስፎርሜሽን እቅድ ተግባራዊ ያደርጋሉ...... የፓርቲውን ስራ አቀላጥፈው ይወጣሉ ተብሎ ሲወደሱና ሲሞካሹ ከነበሩት መሀከል ዋነኛው እና ግንባር ቀደሙ የሆነው የብአዴኑ ከፍያለው አዘዘ በበረከት ስምኦንና በመለስ ዜናዊ ጭምር ታምኖበት ተሹሞ የነበረ ቢሆንም ድንገት ሳይታሰብ የራሱን ቡድን አደራጅቶዋል በሚል ሰበብ ከአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባነት የተነሳ ከመሆኑም በተጨማሪ በአሁኑ ሰዓት የቁም እስረኛ ሆኖ በደህንነት ክትትል ስር መሆኑም ታውቆዋል::

ከኩማ ደመቅሳ በላይ ትልቅ ተሰሚነት የነበረው የብአዴኑ ከፍያለው አዘዘ ወደዚህ ቦታ ተመድቦ ሲመጣ የተለያዩ ስልጣኖችን እንዲጠቀልል ከመደረጉም በተጨማሪ ኩማን በቅርብ ርቀት እየተከታተለ ውሎውን ሪፖርት ለነመለስ እንዲያደርግ ሁሉ በታማኝነት የተመደበ ቢሆንም ሳይታሰብ እና ሳይዘጋጅበት ድንገት የራሱን ቡድን እያደራጀ ከእኛ እጅ ሊወጣ ሲል ደረስንበት በሚል ከስልጣኑ ማባረራቸውን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

በመለስ ዜናዊ በተሰጠ አስቸኩዋይ የግምገማ ሂደት በተደረገው የእርስ በርስ ሙግት አንዱ አንዱን እንዲያጋልጥ እና የሌለበትን ጭምር አሜን ብሎ እንዲያምን ተብሎ ቢዘጋጅም ሁሉም እርስ በርስ መነጋገር ፈርተው የታሰበው ባለመሆኑ በምስጢር በቤተ መንግስት ግቢ በሚገኘው በመለስ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ግምገማው ይደረግ ተብሎ በበረከት ስምኦን መሪነት የተደረገ መሆኑም የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ አስረድቶዋል።

በዚሁ ተደረገ በተባለ ግምገማ  አምስቱም የከተማዋ ባለስልጣናት ላይ በረከት ስምኦን ያዘጋጀው ስንክሳር ጥፋተኛ መሆናቸው ተገልፆላቸው የበለጠ ግን በራሳቸው መንገድ የራሳቸውን ቡድን ፈጥረው እየተንቀሳቀሱ መሆኑ ተደርሶባቸዋል በሚል ሁለት ከብአዴን አንድ ከደኢህዴን የተባረሩ ሲሆን በተለይ ከፍያለው ላይ ግን የተለየ ችግር አለበት ሲልም እንደገለፀ ከምንጮቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል።

መለስ  የገዛ ካድሬዎቹን አላምን ከማለቱም በተጨማሪ ሁለቱን የብአዴን ነባር ካድሬዎች ምክትል ከንቲባው ከፍያለው አዘዘንና የአዲስ አበባ የኢህአዴግ ኃላፊን ልዑልሰገድ ይፍሩን ከስልጣን እንዲወገዱ ከመደረጉም በላይ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በመመሳጠር የራሳችሁን ቡድን አደራጅታችሁዋል በሚል በአዲስ አበባ ከተማ ባሉ ክፍለ ከተሞች ውስጥ የተመደቡ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጭምር በናንተ ስር ተደራጅተዋል ተብሎ ብዙዎቹ የተነሱ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል።

በአሁኑ ሰዓት በየክፍለ ከተማው እና በየቀበሌው በትልቅ ስልጣን ላይ ተቀምጠው የነበሩ የብአዴን ሰዎች ከዚሁ ቡድን ጋር ንክኪ አላቸው እየተባሉ እየተንሳፈፉ ሲሆን አንዳንድ የደኢህዴን እና የኦህዴድ ባለስልጣናትም ተቀጽላ እየተባሉ ከስልጣናቸው  እየተነሱ መሆኑን ምንጮቹ አጋልጠዋል።

በቤተመንግስት ውስጥ በበረከት ስምኦን በተመራው ግምገማ ላይ ኩማ ደመቅሳን ፈሪ..... በስርህ ያሉትን ልትቆጣጠር ያልቻልክ አቅመ ደካማ ......ከመናገር ይልቅ ዝምታን የምትወድ.....ርካሽ ተወዳጅነትን ለማትረፍ የምትጥር.....በሚሉና በመሳሰሉት ቃላት ሲወርድበት የዋለ ሲሆን የደቡቡን ካሚል መሀመድን ደግሞ ተቀጽላ..... እንደ ገደል ማሚቶ የሚሉትን የምትደግም....የጉራጌ ተወላጆችን በምስጢር አደራጅተህ ቡድን የፈጠርክ..... ብሎ እንደሰደበውም የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል።

ግምገማ ተደረገ ከተባለና ስድባቸውን ከቀመሱ በሁዋላ ከአምስቱ ወሳኝ የከተማዋ ባለስልጣናት መሀከል ሶስቱ ማለትም ምክትል ከንቲባው ከፍያለው አዘዘ፤ የአዲስ አበባ የኢህአዴግ ፅህፈት ቤት ኃላፊና ተጠሪ ልዑልሰገድ ይፍሩ ፤የአዲስ አበባ የኢህአዴግ የአባላትና ስልጠና ዘርፍ ኃላፊ የነበረውና የደኢህዴን ባለስልጣኑ ካሚል መሀመድ ሙሉ ለሙሉ ከስልጣናቸው እንዲነሱ ሲደረግ ኩማ ደመቅሳ እና አንደኛው በማስጠንቀቂያ እንደታለፉም የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል።

ምክትል ከንቲባው ከስልጣኑ ከተነሳበት እለት ጀምሮ ተጠባባቂ በሚል  ንጋቱ ዳኛቸው የተባለው የብአዴኑ ሌላ ሰው ቦታውን እንዲረከብ ተደርጎ የነበረ ቢሆንም በዚህኛውም ላይ እነ በረከት እምነት በማጣታቸው የአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊና የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ኃላፊ የሆነውን አባተ ስጦታው የተባለውን በቦታው እንዲቀመጥ ማድረጋቸውን ከምንጮቹ ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል።

ከቀበሌ እስከ ዞን ድረስ ያሉት የአዲስ አበባ ከተማ ባለስልጣናት በተጀመረው ምንጠራ እየታመሱ በመሆኑ ስራ ከመስራት ይልቅ በተስፋ መቁረጥ ስሜት ብቻቸውን እያወሩ ባዶ ቢሮ እየቆለፉ እንደሚቀመጡ የገለፁት ምንጮች አንዳንዶቹ ከስራም ሆነ ከግምገማ እራሳቸውን እየሰወሩ መሆኑ ታውቆዋል::

በተለይ ከተለያዩ ሙያ ላይ ተነስተው በአባልነታቸው ብቻ ለትልቅ ስልጣን የበቁት ሰዎች በተጀመረው ግምገማና ምንጠራ በመሰላቸት ወደ ቀድሞ ስራችን እንመለስ ብለው ጥያቄ እያቀረቡ ሲሆን የአዲስ አበባ የፅዳትና የውበት ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጅ የሆነው ዓለሙ ዘበርጋ ወደ ቀድሞው መምህርነት ስራ መልሱኝ በማለት በገዛ ፍቃዱ ስልጣኑን መልቀቁ ታውቆዋል::

ከላይ ባሉት ባለስልጣናት ላይ የተጀመረው ምንጠራ በተፋፋመበት በዚህ ግዜ በዞን እና በቀበሌ ላይ ሲሰሩ የነበሩ የወያኔ ባለስልጣናት እስከ መጨረሻው ከአባልነት ጭምር ሰርዙን ህዝቡ እንደሆነው እንሆናለን በማለት ኃይለ ቃል እየተናገሩ ከስብሰባ አዳራሽ ጭምር ረግጠው እየወጡ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት የወያኔ ቡድን እጅግ ግራ ተጋብቶ የሚይዘውና የሚጨብጠው ያጣበት ወቅት ላይ መድረሱ ታውቆዋል::

በተያያዘ ዜና በክልል ባለስልጣኖች ላይ የተጀመረው የእስራት እና ከስልጣን የማባረር ዘመቻ ተስፋፍቶ በመቀጠል ለብዙ ዓመታት የቤንሻንጉል ክልል ፕሬዝዳንት የነበረው ያረጋል አይሸሹም ሰሞኑን በሙስና ክስ ፋይል እንደተከፈተበት ተጠቆመ::

የቀድሞ የቤንሻንጉል ክልል ፕሬዝዳንት ነበረውና በአሁኑ ሰዓት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ኃላፊ ያረጋል አይሸሹም በፕሬዝዳንትነት ስልጣኑ ላይ በነበረበት ወቅት የመዘበረው 83 ሚሊዮን ብር ተገኝቶበታል በሚል ሰሞኑን የጸረ ሙስና ኮሚሽን የተባለው በመለስ የሚመራው መስሪያ ቤት ክስ እንደመሰረተበት ታውቆዋል::

የቤንሻንጉል ክልልን በመወከል በአጋር ድርጅቶች ወንበር የተወካዮች ምክር ቤት አባል የነበረው ይሄው ያረጋል አይሸሹም የተባለው የወያኔ ቅልብ ባለስልጣን በምክር ቤት የነበረው ያለ መከሰስ መብቱ እንዲነሳ ተደርጎ ሰሞኑን ለጥያቄ ትፈለጋለህ በሚል ለእስር መዳረጉ ታውቆዋል::

ከ14 ዓመት በላይ የቤንሻንጉል ክልል ፕሬዝዳንት ሆኖ የሰራውና በሁዋላ በፖለቲካ ውሳኔ በመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ ከስልጣኑ የተነሳው ያረጋል አይሸሹም ባለፈው ዓመት ለህክምና ብሎ ወደ አሜሪካ ተጉዞ በነበረበት ወቅት በዚያው ለመቅረት በዝግጅት ላይ እንዳለ የሀገሪቱን የፖለቲካ ገጽታ ታበላሽብናለህ .....የተጀመረውን የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በዓለም ላይ የጀመርነው ዘመቻ ይደናቀፍብናል በሚል በግርማ ብሩ አማካኝነት ተለምኖ ወደ ሀገር ውስጥ ከመጣ በሁዋላ በቁም እስረኛ ነት የቆየ ሲሆን ሰሞኑን ደግሞ በሙስና በሚል ለእስር መዳረጉ ታውቆዋል::

በቢሊዮን የሚቆጠር የሀገሪቱን ሀብት እየጋጠች እና ወደ ውጭ ሀገር እያሸሸች ያለችው የመለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍን እንደልብዋ እየተንፈላሰሰች ባለችበት በዚህ ግዜ አንዳች ትንፍሽ ያላለው የፀረ ሙስና ኮሚሽን የተባለው በመለስ ዜናዊ የሚመራው መስሪያ ቤት በአሁኑ ወቅት የወያኔ የውስጥ ፖለቲካው እየተሸራረፈ በመሄዱና በመዳከሙ የውስጥ እና የዓለም አቀፍ ተቀባይነትን ለማግኘት

ብሎም የመለስን ስልጣን ለማጽናት ሲባል አይጠቅሙኝም የሚላቸውን ባለስልጣናት በሙስና ሰበብ ወደ ዘብጥያ እየከተተ መሆኑና ዘመቻውም ቀጣይነት እንዳለውም እየተነገረ ይገኛል::

ይሄው የወያኔ ባለስልጣን የነበረው ያረጋል አይሸሹም ማክሰኞ ጥቅምት 7 ቀን 2004 ዓ.ም በተደረገ የተወካዮች ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ያለ መከሰስ መብቱ እንዲነሳ ተደርጎ በማግስቱ ረቡዕ ጥቅምት 8 ቀን 2004 ዓ.ም ወደ ማዕከላዊ እስር ቤት መግባቱ ታውቆዋል::

በቤንሻንጉል ክልል ውስጥ የትጥቅ ትግል እያደረገ ከሚገኘው ቡድን ጋር ግንኙነት አለው ተብሎ ከዚህ ቀደም ተገምግሞ እንደነበረ የጠቆመው ዘገባ አሁን ግዜ ጠብቀው በሙስና ሰበብ እስር ቤት ሊከቱት እንደቻለም ተጠቁሞዋል::

በቅርቡ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ባለስልጣናት ላይ የምንጠራ ዘመቻ የተደረገ ሲሆን በተለይ የክልሉን አፈ ጉባኤ እና ምክትል ፕሬዝዳንት ጨምሮ በርካታ የቢሮ ኃላፊዎች ከስልጣናቸው ተነስተው ዛሬ በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ የሚገኙ መሆኑን የጠቆመው ዘገባ ሰሞኑንም የቀድሞውን የቤንሻንጉል ፕሬዝዳንት በሙስና ተብሎ ወደ ዘብጥያ አውርደውታል::

በአሁኑ ሰዓት በወያኔ ባለስልጣናት መሀከል ቡድንተኝነት እየጠነከረና እየተስፋፋ በመምጣቱ የተነሳ ከሀገር ይልቅ መንደር......ከህዝብ ይልቅ እራሳቸውን ....አስቀድመው በጠበበ አስተሳሰብ እርስ በርስ እየታመሱ እንደሚገኙም እየተነገረ ይገኛል::

መለስ ዜናዊ ሰሞኑን በተወካዮች ምክር ቤት ተገኝቶ በሰጠው ማስፈራሪያና ዛቻ ላይ እንዳለው ከሆነ አሁንም የባለስልጣናት እስር እና ምንጠራ እንደሚቀጥል ገልፆ ተረኛው የኦሮሚያ ክልል መሆኑን በይፋ ተናግሮዋል::

የመለስን ማስፈራሪያ ያደመጡ አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት ከሆነ ከዚህ ቀደም ብዙ ሲወራበት የነበረው አባዱላ ገመዳ በቅርቡ ከስራ አስፈፃሚነት የተነሳው እንደ ያረጋል አይሸሹም በሙስና ለመክሰስ ቅድመ ዝግጅት እያደረጉ ይሆናል በማለት አስተያየታቸውን እየሰጡ ይገኛሉ::

የወያኔ ቡድን የከሰረ ፖለቲካውን ለመጠገንና ለማደስ ሲል በገዛ ካድሬዎቹ ላይ የምንጠራ ዘመቻ ከማድረጉም በላይ ሙስና በሚል ታፔላ ዘብጥያ እያወረዳቸው ሲሆን በቅርቡም የናዝሬት የመሀንዲሶች ኃላፊ የሆነው ባለስልጣን ከኃላፊነቱ ተነስቶ ለእስር እንደተዳረገም የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

በዚሁ በተጀመረው የማባረር እና የማሰር ዘመቻ የናዝሬት ከተማ የመሀንዲሶች ሃላፊን ጨምሮ ሶስት መሀንዲሶች የታሰሩ ሲሆን ሌሎች ተፈላጊ ናቸው የተባሉ አራት መሀንዲሶች ስራቸውን ትተው ሀገር ጥለው መጥፋታቸው ተገልፆዋል::

በአሁኑ ወቅት በናዝሬትም ሆነ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ በወያኔ ካድሬዎች ላይ የተጀመረው ምንጠራ ተስፋፍቶ የቀጠለ ሲሆን በቅርቡም ከቀበሌ ገበሬ ማህበር እስከ ወረዳ ድረስ እንደሚዘልቅም የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወያኔ ግራ በገባው በዚህ ወቅት በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝ ለማድረግ ከየክልሉ የመጡ ዶክተሮች አስተዳደራዊ በደሎች እና የመብት ጥሰት እየተፈጸመባቸው እንደሆነ በመቃወም ማስጠንቀቂያ መስጠታቸው ታወቀ::

ከመኝታ ክፍል ጀምሮ እስከ ምግብ አቅርቦት ከፍተኛ በደል ደርሶብናል በማለት በወያኔ ላይ ተቃውሞ ያሰሙት የህክምና ባለሙያዎቹ ማስጠንቀቂያ መስጠታቸውም ታውቆዋል::

አንድ ሀኪም የታመመ ወገኑን አክሞ ለማዳን አስቀድሞ አግባብ ባለው ሁኔታ ጽዳቱ የተጠበቀ መኝታ ክፍል እና ቢሮ ሲኖረው ብቻ ነው ያሉት ሀኪሞቹ እኛ ግን ከመኝታ እስከ ምግብ ከፍተኛ ችግር እየደረሰብን ለዓመታት እየሰራን ከመሆኑም በተጨማሪ ከቀን ወደ ቀን ይሻሻላል ብለን ብንጠብቅም የባሰ ከመቀረፍ ይልቅ እየተስፋፋ በመምጣቱ አደጋው እየገዘፈ በመሆኑ የስራ እና የትምህርት ማቆመ አድማ እናደርጋለን ሲሉ ማስጠንቀቃቸው ታውቆዋል::

ዛሬ ተራ የአንድ ቀበሌ ስራ አስፈጻሚ የተባለ ካድሬ የመኖሪያ ቤት እየተሰጠው.......የወር ደመወዙ ከ5 ሺህ ብር በላይ እየተከፈለው......ለቢሮና ለሌሎች ወጪዎች እየተባለ የደለበ ገንዘብ እየተመደበለት ባለበት በዚህ ግዜ እኛ የወገናችንን ህይወት ለመታደግ ደፋ ቀና እያልን በ2400 ብር ደመወዝ ያለ ሌላ ተጨማሪ ክፍያ ቤት ሳይሰጠን ይባስ ብሎ ለማደሪያ የተሰጠንን ክፍል መንጠቃቸው አሳፋሪና አሳዛኝ ከመሆኑም በተጨማሪ ክብርን የሚነካ በመሆኑ ትምህርቱንም ህክምናውንም እናቋዋርጣለን ሲሉ ማስጠንቀቃቸው ታውቆዋል::

በህክምና ባለሙያዎቹ ማስጠንቀቂያ ስጋት የገባው የወያኔ ቡድን ደህንነቶቹን አሰማርቶ ዋነኛ እና ቀንደኛ አስተባባሪ ናቸው የተባሉትን አምስት ዶክተሮች በተናጠል በስልክና በአካል ማስፈራሪያና ዛቻ እየሰነዘሩባቸው እንደሆነ የጠቆሙት ሀኪሞቹ አሁንም ጥያቄያችን በአስቸኳዋይ ካልተመለሰ የስራማ የትምህርት ማቆም አድማ ማድረጋችን አይቀሬ ነው ሲሉ ጨምረው መግለፃቸው ታውቆዋል::

የያዛችሁትን አቋዋም ካላስተካከላችሁ የከፋ እርምጃ ይደርስባችሁዋል እየተባሉ በደህንነቶች ወከባና ማስፈራሪያ እየደረሰባቸው የሚገኙት እነዚሁ የህክምና ባለሙያዎች በሰጠነው የግዜ ገደብ የጠየቅነው ካልተሙዋላ አሁንም ስራ እናቆማለን ማለታቸው ታውቆዋል::

መኖሪያ ቤት ለማግኘት ካድሬ መሆን አይጠበቅብንም......ሌሎች መሰረታዊ መብቶቻችንን ለማሙዋላት አባል መሆን አያስፈልገንም ያሉት ሀኪሞቹ በህክምና ባለሙያነታችን እና እንደ ተማሪነታችን ማደሪያ ክፍልና ንፅህናውን የጠበቀ ቢሮ ሊሰጠን ሲገባ እንደ አልባሌ የትም ውደቁ መባላችን በእጅጉ ያሳፍራል ሲሉ በምሬት ሲገልፁ ተደምጠዋል::